# ኢትዮጵያን ማስከበርና መጠበቅ በኢትዮጵያዊነት ፅኑ አቋም ተደራጅተን በተግባራዊ አስተዋፅዖ መሰዋዕትነትን በመክፈል ብቻ ነው።

ከበላይ መታፈሪያ ዶ/ር

ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ያለችበትን ችግር፣መከራና ስቃይ ስንመለከትና ስንገመግም እጅግ እጅግ በጣም ውስብስብና አሳሳቢ ሆኖ እናያለን። ኢትዮጵያና ሕዝቧ እየታመሰ፣ብሔራዊ አንድነት ታውኮ፣ሕዝብ ዜግነቱንና የአገር ባለቤትነቱን ተነፍጎ፣ታሪካዊ ክብርና ኩራት ተዋርዶ፣ዳርድንበር ተደፍሮና ለም መሬት እየተሸጠ፤የአገር ብሔራዊ ፍቅርና ስሜት ሲሸረሸርና ሲደበዝዝ ኃላፊነትና ግደታን የሚወስድ፣ አገርና ሕዝብ የሚወክል ሰው የሚሆን የወቅቱ ታሪክ ስሪ መጥፋት የሚያሳዝንና የሚሳሳብ ግደታ እየፈጠረ ነው።

በታሪካዊ የኢትዮጵያ ዜግነት እምነትና ትውልዳዊ ግደታ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ትልቅና ብርቱ ተግባር አለ። ለኢትዮጵና ኢትዮጵያዊያን የሚያስፈልገውን አገርና ሕዝብ ለማዳን መስዋዕትነት ለመክፈል በአህዳዊ ኢትዮጵያ እምነት፣ኩራት፣ ነፃነት፣ ፍቅርና ተስፋ ያለውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በቁርጠኝነትና ፅናት በእጅጉ በአሳሳቢነት የሚጠይቅና የሚጋብዝ በተግባር የሚገለጽ መሪርና ጥብቅ የአገር ጉዳይ ነው።ይህ ደግሞ የአካል፣ የሞራል፣ የውቀት ብስለት ደፋርነትና ጀግንነትን የሚጠይቅ የአርበኝነት ጀብዱ ሥራ ይሆናል።

ዛሬ ኢትዮጵያ በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እጅግ ተዋርዳ፣ተራቁታና ተጎሳቅላ ሕዝቧ መሬት የሌለው ዜግነት አልባ ስደተኛ ሆኖ ትገኛለች።

ወያኔ/ሕውሓትና ሻቢያ በባዕዳን አገሮች ተደራጅተውና ተረድተው በጥፋት መልዕክትነት ከተሰለፉበት ጊዜ አንስቶ በይፋ የሚነዙትም ሆነ በህቡዕ የያዙት ዓላማ አገሪቱን ማዳከምና ማፍረስ፣ በቋንቋ ጎሳ ክልል ሕዝብን በመለያየት እርስበርስ በማናከስ ወደ ማያባራ ጦርነት ውስጥ መክተት ነው።

ወያኔ/ኢህአዴግ ጎጠኛ ፀረ_ ኢትዮጵያ አስተዳደር ኢትዮጵያን ከእናቷ ለሁለት ከፍሎ የውሃ በር አሳጥቶ፣ አገሪቱን በቋንቋ ክልል ሸንሽኖ የኢትዮጵያን ሃብትና ንብረት በመበዝበዝ ለም መሬቷን በመሸጥ፣ ዳር ድንበሯን አሳልፎ ለባዕዳን በመስጠት፣ ያካበተችውን ቅርሶች የተዋዋለችውን ውሎች በማፍረስ፣ ሕዝቧን በገዛ አገሩ ከሥራው፣ ከመኖሪያ ቤቱና ሥፍራው እያፈናቀሉት የሚኖርበትን በቋንቋ ክልል ወስነውበታል። በአገር ጉዳይ በሃቅ የቆሙ ኢትዮጵያዊ ልጆችዋን አድኖ በማሰርና በመግደል እንዲሁም ከአገር እንዲሰደዱና ለከፋ ችግር እንድወድቁ በሕገ_ ወጥ ሕግ አገዛዝ ከባድ ጭቆና እየተፈጸመ ይገኛል። በአጠቃላይ በአገርና ሕዝብ ላይ የጥላቻና የጥፋት ልዮነት መርዝ እየበተኑ ናቸው።

ወያኔ በፀረ _ ኢትዮጵያዊነት የአገሪቱን ሉዓላዊነት፣ የሕዝቧን አህዳዊነትና ታሪኳን ከዷል፣ የሕልውና ምልክት የነፃነት ክብርና ዓርማ የሆነውን አረንጓዴ _ ቢጫ _ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችንን አዋርዷል፣ቀይሮል። ወያኔ/ኢህአዴግ በጠበንጃ ኃይል ለ24 ዓመታት በአምባገነን ፋሽስትዊ ሥርዓት ስፍኖ በቆራጭ ፈላጭ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በመዳፉ ሥር በማዋል፣ የዜግነት፣የመሬት፣ የንብረት ማፍራት ባለቤትነት ተነጥቆ አዋኪ በሆነ የፖለቲካ አየር እንዲታፈግና ተስፋው እንዲመነምን ተደርጓል።

ይህ በዚህ እንዳለ፤ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለሕዝብ ብሶትና ጩኸት ምላሽ ለመስጠት በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በተለያየ የፖለቲካ ድርጅቶች ሥር መሰባሰብ ከጀመሩ ቆይቷል።ዳሩ ግን አብዛኛዎቹ የተፈጠሩት፣ የመረጡትና የተከተሉት የወያኔን የጠባብ ጎጥ ማንነት (የጠባብ አይ ደንቲቲ) ፖለቲካ በመሆኑና ሕዝብን በቅጡ ያላቀፈ፣ያላደራጀና ያልመራ፣ተቃዋሚ ነኝ ፕሮፓጋንዳ ቃላት ብቻ ያላለፈ፣ወያኔን በምርጫ እያጀቡ የሚጌዙና በቂ ሆኖ ሳላልተገኘ ብዙ አገር ወዳድ ለከፍተኛ ጥቃትና ጉዳት ተጋልጠዋል፣ ተስፋ አስቆርጧል፣ በዚህ ሽንፈት የአገር ጥፋትም እየተባባሰ፣ ሕዝብ ለከፋ ችግር እየወደቀ፣ እየተገደለና እየተሰደደ ነው።

የዚህ ዓይነትና የወያኔ ፀረ _ኢትዮጵያ የፖለቲካ አመለካከት ተወግዶ የኢትዮጵያን የብሔራዊ የረጅም ዘመን የሕዝብ አኩሪ ታሪክና የኅብረተሰብ አብሮ የመኖር ባህል፣ወግ፣ፍላጐት፣ ፍቅርና ተስፋውን መሰረት ያደረገ አገር ወለድ ማህበራዊ መዋቅሮችን ከታሪካዊና ምድራዊ አቀማመጥ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያዛመደ፣ ከባዕዳን ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆነ፣ የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም፣ ዳር ድንበር የሚያስከብር አገራዊ ሥርዓት መመስረት ያስፈልጋል።

በዚህ አወንታዊ ሃቅ መሰረት አገር ወዳድ ተቆርቋር የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ጥበብን በመመርኮዝና ፈጣሪ እግዚአብሔርን በመተማመን የሕዝብን ጭቆናና ስቃይ ለማስወገድ፣ለዘለቄታዊ መፍትሄና ብልጽግናን ለማስፈን ታጥቀን መነሳት አለብን።

ወያኔ በፀረ_ ኢትዮጵያ በአገርና ሕዝብ ላይ የዘመተ ባንዳ _ ፋሽስታዊ ጠላት መሆኑን ከተረዳንና ከአወቅን፣ ቀጣዮና ዋና ወሳኙ ተግባራችን ተደራጅቶ በቁርጠኝነትና በፅናት አስፈላጊውን አስተዋፅዖ በማድረግ ጠላትን ድል መንሳት ነው።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጩኸትና ለቅሶ ምላሽ ለመስጠት ታግሎ ለማታገል ሁሉን የሚያስተባብር፣ የሚያደራጅና አቅጣጫ የሚሰጥ በሕዝብ መሀል የሚውል፣ ወያኔ የሚጠላውን ኢትዮጵያ _ኢትዮጵያዊነትን የሚያድስና ኢትዮጵያዊነትን በድል አድራጊነት የሚያቀናጅ እንቅስቃሴ መፍጠር ወቅቱ የሚጠይቀው አጣዳፊ ወሳኝ ተግባር ነው።በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን ዛሬና ታሪክም ሆነ ለመጭው ትውልድ ነፃነትና መብት አስከባሪ የሆነ አቋም መመስረት፣ ትግሉን በፍጥነት በማካሄድ ወያኔ የሚፈጽመውን በደልና ዘረፋ፣ሴራና ተንኰል ለማክሸፍና ኢትዮጵያን ለማዳን ሕዝቧን ነፃ ለማውጣት የሚያስፈልገውን ተቀራርበን ልንመክርበት፣ ልንወያይ የትግል እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ ለመስዋዕትነት መዘጋጀት ወቅቱ ዛሬ አሁን ነው።

የአገሪቱ ሕልውና አጠያያቅ በሆነበት በዚህ ወቅት፣ በዚህ ጊዜ ለአንድት ኢትዮጵያ የቆሙ ዜጎቿና ወዳጆቿ ዘላቂ ጉዳት እንዳይደርስባት ሙሉ ድጋፋችንንና ትብብራችንን ልናሳይና ልንሰጥ ይገባል።አገርና ነፃነት ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህንን አሳሳቢ የፖለቲካ ክስተት እያዬ ዝም ብሎ የሚያልፈው አይሆንም። የዜጎቿን ሁሉ ተሳትፎ የሚጋብዝና የሚአበራታታ የፖለቲካ ሥርዓት መስፈን አማራጭ የሌለው አወንታ ነው።

ለኢትዮጵያ የነፃነት ክብር የእኛ ቀደምት ኢትዮጵያዊያን አጥንትና ደም የፈሰሰባት፣እጅግ ብዙ የሕይወት መስዋዕትነት ለብዙ ዘመናት የተከፈለባት ክቡር አገርና መሬት ዛሬ ሲደፈርና ሲሸጥ የባንዳዎች መፈንጫ ሲሆንና የኅብረተሰብ ባህሪ የማንነት ክብርና ኩራት ሲዋረድና ሲጠፋ ይህ ትውልድ በትዕግስት የሚያልፈው፣ ለነገ የሚባል ወይንም ለሌላ የሚተው ጉዳይ አይደለም።

የአገሪቱ ውድቀትና መደፈር ያሳሰባቸውን በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚያስባስብ፣የሚያደራጅና የሚመራ ሁሉንም ማህበረሰቦች በእኩልነት ያካተተ ኢትዮጵያና ሕዝቧን ስሜትና ፍላጎት የሚያንጸባርቅ፣ አመኔታቸውን ሊያተርፍ የሚችል፤ከሌሎች ድርጅቶች የተለየ የአገርን ክብርና ታላቅነትን አጉልቶና አርቆ ያየና የትውልድ ኃላፊነትን የተቀበለ፣ ጠንካራ ከወያኔ የበለጠና የላቀ፣ የወያኔን ሕገ _ ወጥ ሕገ መንሥት ውድቅ የሚያደርግ ርዕዮተ _ ዓለሙንና ሥርዓቱን ሁሉ የሚያጠፋ አገርና ሕዝብ የሚወክል ሃቀኛና ብርቱ ድርጅት መፍጠር ኢትዮጵያዊነት የሚጠይቀው ፅኑ ሃቅ ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን ! ውርደትንና ሽንገላን የመቀበል ልምድና ባህሪ የሌለን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች እንደ ቀደምት አባት _ እናቶቻችን እምቢኝ ለአሁዳዊ አገሬ፣እምቢኝ ለአንድነቴና ለታሪካዊ ቅርስና ውርሴ፣ ለሰንደቅ ዓላማዬ በማለት የማይታጠፍ ቃል ኪዳን ገብተን በፅናትና በጥንካሬ እብሪት የወጠረውን የትግሬይ ነፃ አውጭ ነኝ ባይ ወያኔ /ኢህአዴግ የባንዳ አገዛዝ ሥርዓትን ማንበርከክና ገፍትሮ ማስወጣት አለብን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው መላ አገሩን፣ስንደቅ ዓላማውን፣ አንድነቱን ፣ ደህንነቱን፣መብቱን፣ እድገቱን፣ ብሔራዊ ግስጋሴውንና ኢትዮጵያዊነቱን ነው።
ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በረጅም ዘመን አኩሪ ታሪክ በሕዝብ የተገነባ ሕልውና ስለሆነ እንኳን ለአገር ውስጥ ለውጭ ወራሪና አስወራሪ ጠላት ያልተበገረና የማይበገር አልፋ _ ኦሜጋ ነው። የርዕዮተ ዓለማችንና የእድገታችን ምንጭና መሰረታችን አገር፣ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት ነው። ወያኔንም ሕልውና አሳጥቶ ድራሹን የሚያጠፋው ኃይል አንድ አገር ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት ነው።ጠንካራ ክንዱና ዋስትናው የአገር ወዳዱና የአንድነት ኃይሉ ኢትዮጵያዊነት ብቻ በመሆኑ ድሉ ምንጊዜም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው

ስለሆነም ከዚህ ኃይል ጋር አሰላለፍን አስተካክሎ መቆምና መደራጀት ብሔራዊ ግደታ ነው። በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የታቀፈ ሰፊ መሰረት ያለው እንቅስቃሴ ማጠናከር፣ አጋሚዶ ባንዳዎችን ደምስሶ የአገርን የግዛት ሉዓላዊነት በአስተማኝ ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ኢትዮጵያን ከዘረፋ፣ከሽያጭ፣ ሕዝቧን ከስቃይና ግድያ ማዳን የዜጎቿ ሁሉ የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው።

ይህን መሰረት በማድረግ ለዚህ ክቡርና ወቅታዊ አገር አድን ዓላማ እውን መሆን የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ልብና ፍላጐት፣ ድጋፍና ትብብር በጥልቅ በመተማመን አገር ወዳዱና ትውልድ አክባሪው ሁሉ ኢትዮጵያን በዓለም ፊት እንደ ታሪኳ ታላቅነትና ክብር ልንጠብቅ፣ሕዝቧን ነፃ ለማድረግ ይህ ትውልድ ኃላፊነትና ግደታ ያለበት ስለሆነ በልበ ሙሉነት አሞቱን ኮስተር አድርጐ በሕዝብ መሀከል ገብቶ በመሰማራት፣ በአዝማችነትና በደጀንነት ለተግባር እንዲንቆም፣ በአገርና በሕዝብ ስም እጠይቃለሁ።

ለዚህ ጉዳይ ለመወያየት በ <belay211@gmail.com> ያግኙን

## ኢትዮጵያ በእውነት፣ በሃቅ በቆመ ሕዝብ ድል ታደርጋለች ! !

## ምንጊዜም ኢትዮጵያ አሸናፊ ናት ! !

ታህሳስ 29/2007